# ኑረሃል

ወንዞ ጓራችን ሲፈስ
የተስፋይቱ ሃገር ስንደርስ
ለምኑ እናልቅሰ
ፅላታችንን ለትመለስ።

ኑሮሃል
ህዝብህን ዳኝተሃል
ዕረፍት ይገባሃል።

እትብትህ ዓድዋ ሥላሴ
ግባአተ መሬትህ ቅድሰተ ሥላሴ
ታሪክህ ከሥላሴ ወደ ሥላሴ
ዕጣህ ሆነና ልትቀይስ ህዳሴ።

ኑረሃል
ለወገንህ ተከራክረሃል
ዕረፍት ይገባሃል።

ጀመርክ ጉዞህን በንግስተ ሳባ
ቀጠልክ በአዲስ አበባ
ወንጌትም ነበረ
ደደቢትም አልቀረ።

ኑረሃል
ላገርህ ተዋግተሃል
ዕረፍት ይገባሃል።

ኢትዮጲያዊው አዳም ስሚዝ
ህዝብህ በችግር ሲቅበዘበዝ
ለመጪው ትውልድ መሰረት ስታኑር
አራሹ ተጎናፀፈ ክብር።

ኑረሃል
ስነጥበብን አጥንተሃል
ዕረፍት ይገባሃል።

ታገልክ ሙስና ለመቀነስ
የማይታይ ጠላት ለመደምሰስ
ተራራው ላይ ሳይደርስ
ታድያ ለምኑ ላለቅስ።

ኑረሃል
ለወገንህ ገብረሃል
ዕረፍት ይገባሃል።

የተራቡትን ተመልክተሃል
ለታመሙትም ወጌሳ ልከሃል
ላመንክበት ቁመሃል
አባይንም ደፍረሃል።

ኑረሃል
ለዓላማህ ቁመሃል
ዕረፍት ይገባሃል።

ሙቅም ነህ በራድም ነህ
ግን ለብ አይደለህ
አንተ’ማ ያው አንተ ነህ
ምንጊዜም ከህዝብህ ትኖራለህ።

ኑረሃል
ወጣቱን አስተምረሃል
ዕረፍት ይገባሃል።

ቁብብሎሹን ተቀበሉህ
ወጣቱ ወሰደዉ በተርህ
ጀምረዋል ልጆችህ
ትንሳኤ ሲኖር ታያለህ።

ሃይለ ዘፈረፅዮን

Arcadia, CA 8/17/2013